# የሽግግር መንግሥት ወይስ
# የሽብር መንግሥት?

አንድ የሀገራችንን ፖለቲካ ለብዙ ዓመታት የተከታተሉ አዛውንት በፖለቲካው መድረክ ስለሚርመሰመሱት አድር ባዮች በቀልድ ሲያጫውቱ እንዲህ አሉ ይባላል። "ዛሬ ዶ/ር ኮሎኔል አቢይ፣ አዲሱ ጠ/ሚር በሚለቃቸው ማራኪ ንግግሮች ተመስጠውና ስክረው ተደመሩ እንደመር እያሉ የሚያዋክቡን የድል አጥቢያ አድር ባይ ፖለቲከኞች በወንዝ ዳር ለምልሞ እንደሚበቅል ቀጤማ ናቸው። በወንዝ ዳር የሚበቅል ቀጤማ በክረምት ውሃ ሲሞላ በጎርፉ ኃይል ከስሩ ተመንግሎ ባይወጣም ለሽ ብሎ ይተኛል። ግማሹም ጎርፉ ይዞ በሚያመጣው አፈርና ጭንጫ ወይም አሸዋ ተቀብሮ ይቀራል። በአንጻሩ ግን በወንዙ ዳር የሚበቅል ቀርከሃ ወይንም ሸንበቆ የውሃው ሙላት የቁመቱ ግማሽም ድረስ ቢውጠው እንደቆመ ይታያል። የዋሃው ሙላት ካለፈ በኋላም ለብዙ አገልግሎት ይውላል።" ለነገሩ ቀጤማ የውሃው ሙላት ከጥቅም ውጪም ባያደርገው ያው ዞሮ ዞሮ አገልግሎቶ ለቤት ጉዝጓዝነት ነው። እንዲያው አድር ባይ ወዲህ ቢሉት ወዲያ ጊዜውን ጠብቆ መጎዝጎዙና ማፈረሪያነቱን ማሳየቱ አይቀሬ ነው ለማለት ነው። ከመቆየት፣ ከዕድሜ መማር ያልቻለውን አድርባይ ሁሉ ስንመለከት ደግሞ አድርባይነት የተፈጥሮ ይሆን? ብለን እንድንጠይቅ ያደርገናል።

ታዲያ በሀገር ቤትም ሆነ በዲያስፖራው አቢይ ነብያችን በ 100 ቀናት ውስጥ ያመጣው ለውጥ ከምንችለው በላይ ስለሆነብን የሚያስፈልገው የድጋፍ ሰልፍ ብቻ ነው በማለት እንደ ቀጤማው ለሽ ብለው ሌላውም ለሽ ብሎ እንዲተኛ የሚርመሰመሱትን እየታዘብን ነው። በዲያስፖራ ከብራስልስ እስከ ሎስ አንጀልስ የድጋፍ መልዕክቶችና የስብሰባ ጥሪዎች በሽበሽ ሆነዋል። ከዚህ ጽሑፍ በታች አንዳንዶቹን አቅርበናል።

በሌላ በኩል ደግሞ በድጋፍ ሥካር ሳያብዱ ያሁኑን ወቅት የሕዝቡ አመፃ ግፊት ያመጣው ውጤት መሆኑን ተገንዝበው፣ የሕዝቡ ትግል ውጤት ደግሞ ለሦሥተኛ ጊዜ እንዳይቀማ ወይንም አቅጣጫውን እንዳይስት ሁሉን አቀፍ የሽግግር መንግሥት አሁኑኑ እንዴትና ለምን የሚለውን ሲያብራሩ ይደመጣሉ። ለምሳሌ በቅርቡ ከእሥር የተፈቱት አቶ እስክንድ ነጋ ስለሽግግር መንግሥት ያቀረቡትንና ኢሕአፓ በልሣኑ ዴሞክራሲያ ስለ ሽግግር መንግሥት ያስተላለፈውን አባሪ አድርገነዋል። እነዚህ ደግሞ ጥቂትም ቢሆኑ በውሃው ዳር እንዳለው ቀርከሃ ማለት ናቸው። የአብይ ጎርፍ ሲያልፍ ቀጥ ብለው የሚቀሩ ዕውነታዎች። እናም ድረ-ገጻችን በዚህ ዓምድ ባለፉት 40 እና 50 ዓመታት በሀገራችን ፖለቲካ በተደጋጋሚ በችኩል አድር ባዮች ዴሞክራሲያዊ ሕዝባዊ ስርዓት እንዳይመጣና አምባገነኖች የሕዝቡን ትግል ውጤት ሞጭልፈው በሥልጣን ኮርቻ ላይ እንዲደላደሉ ያደረጉባቸውን የጥፋት ታሪካቸውን ስለምናስታውስ የአሁኑን ወቅት ሁሉም ኢትዮጵያዊ ቆም ብሎ በረጋ መንፈስ ምን መደረግ አለበት በሚለው ላይ እንዲመክር ለማመላከት ነው። ሁሉም መደመር ያለበትም ሆነ መደመር የሚችለው ከሕዝቡ ወገን ሲሆን ብቻ ነው። አዲሱን ጠቅላይ ሚኒስቴር ጨምሮ! በሰከነ ሁናቴ ማሰብ ካልቻልን የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል እንዲሉ እኛም ይዋል ይደር እንጂ ከዚህ በፊት እንደተሸወድነው የሽብር መንግሥት መሠረት ሆነን ቁጭ ነው። ስለሆነም ሁሉን ያቀፈ የሽግግር መንግሥት አሁኑኑ!

# የሽግግር መንግሥት ጥያቄ የሞት እና የሽረት ጥያቄ ነው = ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ

July 22, 2018 – Konjit Sitotaw — Comments ↓

"የሽግግር መንግሥት ጥያቄ የሞት እና የሽረት ጥያቄ ነው"

ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ሀገር ቤት ከሚታተመው ግዮን መፅሄት ጋር ከአሜሪካ መልስ ያካሄደው ቃለ-ምልልስ!!

በመጀመሪያ ነፃ ምርጫ ለማድረግ ነፃ ተቋማት ያስፈልጋሉ፡፡ ነፃ መደረግ ያለባቸው ተቋማት ሁሉም በገዥው ፓርቲ ቁጥጥር ስር ናቸው፡፡ ይህንን አንባገነን ስርዓት ተቋማቱን ከራስህ ስር አፅዳ (ነፃ አድርጋቸው) ብለን ተልኮ ልንሰጠው አንችልም፡፡

ባለፉት 27 አመታት በግልፅ እዳየነው ኢህአዴግ እንደልቡ ሲያሽከረክራቸው በኖረበት ሁኔታ፤ እንዴት 'ኢህአዴግ እራስህን አፅዳ' ብለን ልናዘው እችላለን? ምናልባት በሆነ አጋጣሚ ስልጣን ላይ የነበረው ግንቦት 7 ቢሆን፤ ግንቦት 7ን ከግቦት 7 አፅዳ ብለን በተመሳሳይ ተልኮ ልንሰጠው አንችልም፡፡

ስለዚህ ሁሉም ተግበስብሶ ሳይሆን ዋና ዋናዎቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሳተፉበት የሽግግር መንግሥት ይቋቋም እና እነዚህ ነፃ መሆን ያለባቸውን ተቋማት ነፃ አድርጎ ካላደራጀ መቸም ቢሆን ነፃ ምርጫ ማድረግ አይቻልም፡፡

የሽግግር መንግሥት ጥያቄ የሞት እና የሽረት ጥያቄ ነው፡፡ የዴሞክራሲ ጥያቄ ነው፡፡ ያለሽግግር መንግሥት የትም መራመድ አይቻልም፡፡ ይህ ኢህአዴግን የመጥላት የማዋረድ ጥያቄ አይደለም፡፡ ይህ አብይን የመውደድ እና የመጥላት ጥያቄ አይደለም፡፡ ነፃ እና ፍትሀዊ ምርጫ ለማድረግ የግድ የሚያስፈልጉትን ነፃ ተቋማት ለማቋቋም እና ለማፅዳት የሽግግር መንግሥት የግድ ስለሆነ ነው፡፡

ነፃ ተቋማት ስንል ምርጫ ቦርድን ብቻ አይደለም፡፡ ነፃ ተቋማት ደህንነቱን፣ ፖሊሱን፣ መከላከያውን ያካትታል፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ ህዝብን በቀጥታ የሚያገለግሉት የከተማ እና የገጠር ቀበሌዎች ስለሆኑ፤ በምርጫም ውስጥ ትልቅ አፍራሽ ሚና ስለነበራቸው ነፃ የግድ ነፃ መደረግ አለባቸው፡፡ አብይ መራውም አልመራውም ይህንን የቤት ስራ ለኢህአዴግ ልንሰጠው አንችልም፡፡

★ዴሞክራሲያ★

ዴሞ ቅጽ 43 ቁ.4 መጋቢት/ሚያዚያ 2010 ዓ.ም

## ሕዝባዊ ትግልና የሽግግር ጥያቄ

ከአለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ ዘረኛውንና አምባገነኑን የወያኔ አገዛዝ ለማስወገድ፤ ብርቱ መሥዋዕትን ያስከፈለ ሕዝባዊ ዐመፅ ተካሄዷል። በተለያዩ አካባቢዎችና በልዩ ልዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ጠበብ ያሉ ጥያቄዎችን በማንሳት የተጀመረው ሕዝባዊ የተቃውሞ እንቅስቃሴ በሂደት አድማሱን አስፍቶና በርካታ ታጋዮችን አካትቶ የትግሉን ዒላማ አገዛዙን ወደ ማስወገድና ሥርዓቱን ወደ መለወጥ አሳድጎ የሞት የሽረት ግብ ግብ በማካሄድ ላይ ይገኛል። የትግሉ ግብ ገና ከዳር ባይደርስም በየአካባቢው የተካሂዱት ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች፣ አድማዎችና ዐመጾች አገዛዙን አሽመድምደውታል፤ አከርካሪውን መትተው አዳክመውታል፤ በትዕቢት የተወጠረውን ቡድን በተከላካይ ድባብ እንዲሸበብ አድርገውታል። በየጊዜው እያደገ በመጣው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ምክንያት ገዥው ክፍል በውስጥ መከፋፈልና መሰንጠቅ ደርሶበታል፤ ያልተቋረጠ ግምገማ እንዲያካሄድ ተገድዷል፤ ጥፋተኛ ነን ብሎ በይፋ ወንጀሉን ለመናዘዝ በቅቷል።

የኃይል ሚዛኑ ከአገዛዙ ወደ ሕዝቡ እያጋደለ መምጣቱንና በመጨረሻም የዐመፁ ጎርፍ ጠራርጎ እንደሚወስደው በሚገባ የተረዳው የወያኔ ቡድን ራሱን ከጎርፉ ማዕበል ለመከላከልና የሥልጣን ዘመኑን ለማራዘም አዘናጊና አደናቃፊ እርምጃዎችን አጠንጥኖ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል። በከፍተኛ ግለት እየተቀጣጠለ የነበረውን ሕዝባዊ ዐመጽ ቀዝቃዛ ውሃ ደፍቶ ለማቀዝቀዝም ሆነ አንገቱን ከልቶ እስከናካቴው ለማስወገድ፤ በአንድ በኩል በሕዝብ ተጠልቶ የነበረውን መሪ ተብየውን አውርዶ የሕዝብ ቋንቋ በሚናገርና ያልተጨበጠ ተስፋ በሚሰንቅ ሌላ ጠቅላይ ሚኒስትር ሲተካ በሌላ በኩል ዐመጹን በኃይል ለመደምሰስ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አውጇል። በአዲሱ የወያኔ መሪ አማካኝነት በርካታ የአስተዳደር ለውጦችና መስተካከሎች እንደሚደረጉ፤ የተሟላ ዴሞክራሲ እንደሚኖር፤ ነጻ ምርጫ በተግባር እንደሚውል፤ ...ወዘተ እየተለፈፈ በሌላ በኩል በኮማንድ ፖስት አማካይነት ታጋዮች እየተለቀሙና እየተገደሉ ትግሉን ለማኮላሸት ከፍተኛ ጥረት ሲደረግ እያየን ነው። ጠቅላይ ሚኒስትር ተብየው በዚያው በድርጅቱ የተሰየመ መሆኑ ግልጽ ቢሆንም የሥልጣን ሽግግር ተደረገ በሚል ከበሮ እየተደለቀ፤ በተለያዩ ስብሰባዎች ላይ ምርጥ ምርጥ ቃሎች በመጠቀም ያልሆነ ተስፋ እየተሰጠ፤ አባላት በአዲስ መልክ እየተመለመሉ፤ በዲያስፖራው ሳይቀር ይህንን ጉዳይ የሚያሳኩ ክፍሎች ተልእኮ እየተሰጣቸው የሕዝብን የትግል መንፈስ ለማሽሽ የሚደረገው እንቅስቃሴ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ነው። በሌላ በኩልም የወያኔው ቡድን ድርጅታዊ አቋሙን እያጠናከረ፤ ለጥቅም ያደሩትን በአዲስ መልክ እየመለመለ፤ በወታደሩና በጸጥታው በኩል ተከስቶ የነበረውን ክፍተት እያሟላ ለሌላ ዙር የአምባገነን አገዛዙ ሁኔታውን እያመቻቸ መምጣቱ የሚታይ ሆኗል። በጻዕረ ሞት ላይ የሚገኘው አገዛዝ የኋላ ኋላ መወገዱ የማይቀር ቢሆንም፤ በሚወስዳቸው ጥገናዊ የማስመሰያ ለውጦች የዜጎችን አስተሳሰብና አስተያየት ለማስለወጥና ከትግሉ ለማዘናጋት በከፍተኛ ደረጃ በሁሉም መስክ እየጣረ ነው።

አምባገነንና አፋኝ የሆነው የወያኔ የአገዛዝ ሥርዓት ሙሉ በሙሉ ተወግዶ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ካልተተካ በስተቀር፤ የሀገራችን ሥር የሰደደ ችግር ይፈታል ተብሎ የሚታሰብ አይሆንም። አዲስ ጠቅላይ ሚኒስትር ከመሾም ጀምሮ በተከታታይ ይወሰዳሉ ተብለው በአገዛዙ በዲስኩር መልክ የቀረቡት እቅዶች ሥልጣን ለማራዘሚያ የተቀየሱ ሴራዎች ናቸው እንጅ ሥርዓቱን አስወግደው መሠረታዊ ለሆነው የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በር የሚከፍቱ አይደሉም። አሮጌውን ጠቅላይ ሚኒስትር አውርዶ በአዲስ የተካው የወያኔው ጭምብል ኢሕአዴግ መሆኑ እየታወቀና የሹመቱ ዝውውር በአንድ ድርጅት ውስጥ ባሉ ግለሰቦች መካከል መሆኑ ግልጽ ሆኖ እያለ የሥልጣን ሽግግር ተደረገ ተብሎ ከበሮ እየተመታለት ያለው ዘፈን ቢበዛ ከተራ ቀልድ ሊያልፍ አይችልም። ላለፉት 27 ዓመታት የመንግሥት ማዕከል የሚባለውን የወታደሩን የጸጥታውንና የፍርዱን ተቋም እንዲሁም ቢሮክራሲውን ተቆጣጥሮ ኢሕአዴግ የሚባለውን ጭምብል እንዳሻው የሚነዳው የወያኔው ድርጅት በመሆኑ ተሰየመ የተባለው ጠቅላይ ሚኒስትር የዚህ የድርጅት ፖሊሲ አስፈጻሚ እንጅ በግሉ የሚያቀርበውም የሚያስፈጽመውም ፖሊሲ የለም። ግለሰቡ ድርጅቱ ለሚመራበት ለዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነትና ለአብዮታዊ ዴሞክራሲ መርህ ተገዥ በመሆን የወያኔን ፖሊሲ ለማስፈጸም ኃላፊነትና ግዴታ አለበት። የተለየ ሰብዕና አለው ቢባል እንኳ የራሱን ፖሊሲ ለመቀየስም ሆነ ተግባራዊ ለማድረግ አቅሙም ሆነ የሥልጣን መሠረት የሌለው መሆኑ ግልጽ ነው።

የወያኔ አገዛዝ ተንከባሎ ለመውደቅ አፋፍ ላይ በደረሰበት በአሁኑ ወቅት በአንድ በኩል አገዛዙን ከመጠን በላይ አግዝፈው የሚያዩና በሕዝባዊ ትግሉ ምንም ተስፋ የሌላቸው ወገኖች፣ በሌላ በኩል ወያኔ የሚወስደውን የማዘናጊያ እርምጃዎች በመንተራስ ለወያኔው አምባገነን አገዛዝ ህይወት ለመስጠትም ሆነ ራሳቸውን ሥልጣን ላይ ለማስቀመጥ የቋመጡ ክፍሎች የተለያዩ ሀሳቦችን ሲሰነዝሩ ይደመጣሉ። በአዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር አማካይነት ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሽግግር ማድረግ ይቻላል ከሚሉት ጀምሮ፤ በምርጫ ሂደትና በአስፈጻሚ አካሎች ላይ የተወሰነ ጥገናዊ ለውጥ ከተደረገ ተቃዋሚ ኃይሎች በምርጫ ሥልጣን ሊይዙ የሚችሉበት መንገድ ሰፊ ነው በማለት እየተቀነቀኑ ያሉ ሀሳቦች ሐቅ ጋር የተጣሉ፤ መሠረታዊ ጭብጥነት የሌላቸውና ከማይጨበጥ ምኞት ወይም ከሥልጣን ጥማት የሚመነጩ ናቸው።

የወያኔው ቡድን የሚቆጣጠራቸው የወታደራዊና የፀጥታ ተቋማት እንዳሉ ሆነው ነፃ የሆነ ሽግግር ይካሄዳል ማለት ተጨፈኑና እናታልላችሁ ከማለትና የወያኔን አገዛዝ፤ አስመሳይ ቀለም ቀባብቶ ዘረኛ ሥርዓቱን እንዲቀጥል ከመፍቀድ ውጭ ሌላ መልዕክት አያስተላልፍም። በአሸዋ ላይ የተገነባውን ዘረኛ የአገዛዝ ግድግዳ፣ በሽንብራ ግርፍ ለስኖ፤ ለሳስኖና አውሸልሽሎ የሥልጣን ዕድሜውን ለማስረዘም የተቃጣ ሙከራ እንደሆነ መቆጠር አለበት። የሕግ አውጭና ተርጓሚው ተቋማት ፤ በፈላጭ-ቆራጭ ዕዝ ወድቀው፤ አፋኝና ገዳይ ደንቦችና ህግጋት ሳይወገዱ እንዳሉ ሆነው የሽግግር መንግሥት ተቋቁሞ ሠላማዊ ሽግግር እውን ይሆናል የሚሉ ራሳቸውን ከማታለል አልፈው ተርፈው፤ ወቅታዊ ጥያቄዎችን የሚያዳፍኑ ናቸው። የኢትዮያን ሕዝብ መሠረታዊና እስትራተጂያዊ ወይም ዘላቂ ጥያቄዎች አቅጣጫ ለማሳት የተቃጡ ጥረቶች ናቸው።

በአንድ ቡድን ቁጥጥርና የበላይነት ስር ያሉት መንግሥታዊ ተቋማት መሠረታዊ ለውጥ ሳይደረግባቸው፤ የዕርቅ ስብሰባ በማድረግና፤ አንተም ተው አንችም ተይ በመባባል ሀገሪቱ ከገባችበት ችግር ወጥታ ወደ ዴሞክራሲያዊ ሽግግር ልታመራ ትችላለች ብለው የሚመኙ አሉ። ምኞትን ወደ ተጨባጭ እርምጃ ለመተርጎም ግን መነሻን በሐቅ ላይ አድርጎ

መንቀሳቀስ ያስፈልጋል። አሁን የሚታየው የወያኔ ግትር አቋም ካልተነፈሰ በስተቀር ፤ ወያኔ ወደ ክብ ጠረጴዛ ሊመጣ የሚያስገድደው ሁኔታ ተፍጥሯል ማለት የሚቻል አይደለም። ተገዶ መምጣቱ ግን አይቀርም። ተገዶ ለመምጣት የሚጣደፈው፤ በሁለንተናው ዘርፍ፤ ዕርቃን-ሥጋውን ሲቀር ብቻ ነው። በወቅቱ ሁኔታ፤ መንግሥትን መንግሥት የሚያደርጉትን የኢኮኖሚውን፣ የማኅበራዊውን፣ የፖለቲካውን፣ የፀጥታውን፣ የሀገርና የውጭ ንግዱን፣ መከላከያውንና ፕሮፓጋንዳውን ፤ የመጨቆኛ ተቋማትንና መገልገዮቹን ሁሉ ሳይቀር አጠቃሎ ተቆጣጥሯል። የዕምነትና የትምህርት መስጫ ተቋማትንም ሰርስሮ ገብቶ አፍኗቸዋል። በሀገሪቷ፣ ከሰማይ በታችና ከምድር በላይ ተፎካካሪ በሌለው ዘዴ ማንም በማይሻማውና በማይተናኮለው መንገድ በፍጹማዊነት ሁሉንም በእጁ አስገብቷል። ይኸ ዕውነታ በገሀድ በሚታይባት ሀገር፤ ወያኔ ለእርቅና ሠላም ያስባል ብሎ መመኘት ከንቱ ነው። እስከዛሬ እንዳየነው፤ ስንቶቹ ሕዝብን ከድተው ቢለምኑትም በእምቢታ አሳፈራቸው እንጂ ስምምነቱን አልቸራቸውም። ትላንትም ሆነ ዛሬ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ መሠረታዊ ጥያቄ ፤ ሥር ነቀል የሆነ መሠረታዊ ለውጥ እንጅ የጥገና ለውጥ አይደለም። ይህ ጥያቄ በአግባቡ አስካልተመለሰ ድረስ፤ ሕዝባዊው ዐመፅ ይቀጥላል እንጅ አይቆምም። ሊያቆመው የሚችልም ምድራዊ ኃይል ሊኖር አይችልም።

ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ከአንድ ገዥ ቡድን በሚደረግ ችሮታ ወይም መልካም ፈቃድ የሚገኝ አይደለም። ህያው ሆኖ ለዘለቄታ ሊቆይ የሚችለውም በአንድ ገዥ ቡድን ፍላጎት ወይም በጎ ምኞት ሊሆን አይችልም። ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሕዝብ ትግል ውጤት ነው፤ ህልውናውን አስፍኖ ለዝንተ ዓለም ተጠናክሮ ሊቆይ የሚችለውም በሕዝብ ተሳትፎና ትብብር እንዲሁም ተከላካይነትና ዘበኝነት ነው። ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን እውን ለማድረግ በመጀመሪያ የአምባገነኑን አገዛዝ የመጨቆኛ መሣሪያ ማምከን ያስፈልጋል። አምባገነኑ ኃይል መሠረት ያደረገውን ኃይልና ሥልጣን ወደ ሕዝብ ማዛወር ያስፈልጋል። አምባገነኑ አገዛዝ ከሥልጣኑ ከተወገደ በዴሞክራሲያዊ የሽግግር ሂደት ሕዝቡ የሥልጣን ባለቤት የሚሆንበትን መሠረት መገንባት ይቻላል።

> ለዴሞክራሲ ሥርዓት የሚደረገው ሽግግር እንዴት ይመጣል ? ዓላማው ምንድን ነው? ሂደቱስ ምን ዓይነት መልክ ይኖረዋል? ተግባራቱስ ምን ድን ናቸው? እነማን ይሳተፉበታል? ተልዕኮውስ ለምን ያህል ጊዜ ይሆናል የሚሉት መልስ የሚያስፈልጋቸው ወሳኝ ጥያቄዎች ናቸው።

አምባገነን አገዛዞች በሕዝባዊ አመፅ ወይም በመፈንቅለ መንግሥት ሲወገዱ፤ የሽግግር ጥያቄ ሁልጊዜ ይነሳል። አምባገነን አገዛዝ አከርካሪው ተመትቶ ለሕዝባዊው ዐመፅ ካልተንበረከከ፤ የሽግግር ጥያቄ ሊነሳም ተግባራዊም ሊሆን አይችልም። ለረጅም ዓመታት በአምባገነን እስር ቤት ሲማቅቅ የነበረውን ሕዝብ ፤ እስከወዲያኛው ነፃነትና ፍትሀዊ መብት ለማጎናፀፍ፤ የከበበው አጥር መፈራረስ ይኖርበታል። የሚጓዝበት ጎዳና መጠረግ አለበት። ዴሞክራሲያዊ ሽግግር፣ መጭው ትውልድ፣ እስከ ዝንተ-ዐለሙ፤ በማንኛውም ጊዜ ከሚነሳ አምባገነን ወታደራዊ ኃይል ሆነ አስመሳይ ቡድን መብቱን ለሚጠብቅበት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መሠረት የሚጥል፤ መንገዱን የሚያስተካክልና የሚጠርግ ክስተት ነው። ስለሆነም የሽግግሩ ዐብይ ዓላማ ፤ የአገሪቱ የወደፊት ዕድል በአንድ ነፍጥ በታጠቀ የፖለቲካ ቡድን እጅ በድጋሚ እንዳይወድቅ ለማድረግና ወሳኙና አድራጊ-ፈጣሪው ሕዝብ ብቻ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው።

ይህንን ለማድረግ፤ ቢያንስ ሁለት ወሳኝ ዕርምጃዎችን መውሰድ ይጠይቃል። አንደኛው፤ ለዓመታት አምባገነን ሥርዓት ገንብቷቸው የነበሩትን አፋኝ ሕጎች ፤ ተቋማትና መዋቅሮችን ማፈራረስና ዴሞክራሲያው ባህርይን ባጠለቀ አዲስ መልክ ማዋቀር። ሁለተኛው ደግሞ፤ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መሠረት ሊሆኑ የሚችሉት የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በቋሚነት ሊጠበቁ የሚችሉበትን፤ ነፃነት ሊጠበቅ የሚችልበትን00፤ ሕዝብ የሥልጣን ምንጭና ባለቤት የሚሆንበትንና ድምፁ በሚገባ የሚከበርበት ሁኔታን ማመቻቸት፤ ተቋማትንና መዋቅሮችን መገንባት፤ ለዴሞክራሲያዊ የሥልጣን ሽግግር መሠረት የሚሆኑ ሁኔታዎችን መፍጠር፤ ከሕገ መንግሥቱ ጀምሮ ከሕዝቡ ፍላጎት ውጭ የተካተቱ የሕግ አንቀጾችን በሕዝብ ምርጫና ይሁንታ እንዲወገዱ ማድረግ፤ የወታደሩንና የፀጥታውን ተቋማት ተዋጽኦና ሚዛናዊነት ሀገራዊ መሆናቸውን መጠበቅና ከማንኛውም የፖለቲካ ቡድን ቁጥጥር ውጭ እንዲሆኑ ማድረግ ነው። ይህ እውን ሲሆን ብቻ ነው፤ በዕርግጥም በአገሪቱ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሰፍኗል ማለት የሚቻለው።

በሽግግር ሂደት ወቅት የሚመሠረተው የሽግግር መንግሥት ካለበት የኃላፊነት ተግባራት አንዱና ዋነኛው፤ የአምባገነኑ ኃይል ሲወድቅ፤ በአገሪቱ ውስጥ የሚፈጠረውን ያስተዳደር ክፍተት በመሙላት፤ ሠላም እንዲሰፍን፤ ሕግና ሥርዓት እንዲከበር፤ ማድረግና የአገሪቱን የዕለት-ተዕለት አስተዳደራዊ ተግባራትን ማካሄድ ነው። ተግባሩና ኃላፊነቱ ግን በዚህ የተወሰነ አይደለም። የወያኔ አምባገነን አገዛዝ ከተወገደ በኋላ መጀመሪያ የሚነሳው ጥያቄ፤ ሕገ-መንግሥቱ ምን መሆን አለበት ? የሚለው ነው።

ለአለፉት 27 ዓመታት በሥራ የዋለው የወያኔ ሕገ-መንግሥት በወያኔ የተቀረፀ (ባንዳንድ አስመሳይ አንቀጾች የተቀባባ ቢሆንም) የወያኔ የፖለቲካ ፕሮግራም ከመሆኑ በላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃ በሆነ ሁኔታ ያላፀደቀው መሆኑ ግልፅ ነው። ስለሆነም፤ በመጀመሪያ፣ ሕገመንግሥቱ እንዳለ ይቀጥል አይቀጥል ወይስ ይቀየር? ከተለወጠስ ለውጡ ምን ምንን ማካተት አለበት? የሚሉት ጥያቄዎች በሕዝብ ውይይትና ይሁንታ መልስ ማግኘት አለባቸው። የመገንጠልን መብት የሚፈቅደው አንቀፅ 39 እና ለበርካታ ዜጎች ህይወት መጥፋት ሆነ፤ ከቤት ንብረታቸው መፈናቀል ምክንያት ከመሆን አልፎ የኢትዮጵያን ህልውና አደገኛ ሀኔታ ላይ ያደረሰው በጎሳ ላይ የተመሰረተው የክልል አገዛዝ ለሕዝባዊ ውይይትና ውሳኔ መቅረብ አለባቸው የሚለውም የበርካታ ዜጎች አስተያየት መሆኑ መሰመር አለበት። ሕገ-መንግስት ተብዬው ሰነድ ለወያኔ እንዲያመች ተብሎ የወጣ በመሆኑ መቀየሩ የማይቀር መሆኑን አብዛኛው ሕዝብ ያምናል።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፤ ምን መልክ መያዝ አለበት? አስተዳደሩስ ፕሬዜዳንታዊ የአስተዳደር ወይስ በጠቅላይ ሚኒስትር የሚመራ የአስተዳደር ሥርዓት ይሻላል? የሚሉት ሊነሱ የሚችሉ ጥያቄዎች ሲሆኑ፤ አሁንም በሕዝብ ውይይትና በሕዝብ ውሳኔ ለዘለቄታው መፍትኄ ሊሰጣቸው ይገባል። የሽግግሩ መንግሥት ፤ ከሕግ ዐዋቂዎችና ተመክሮ ካላቸው እንዲሁም በሕዝብ ከተመረጡ ዜጎች የሚውጣጣ የሕገ-መንግሥት አዘጋጅ ጉባዔ መመስረትና በዚህ አካል አማካኝነት የሚቀርቡ ማሻሻያዎች በሕዝብ ውይይትና ውሳኔ -ሕዝብ እንዲፀድቅ ማድረግ ኃላፊነት አለበት።

የወታደሩና የፀጥታው ክፍል ነፃና ገለልተኛ የሚሆንበትን መንገድ ማመቻቸት ነው። ወያኔ ሥልጣን ከያዘ ጀምሮ፤ የወታደሩን እና የፀጥታውን ተቋማት በቁጥጥር ስር አድርጎ የፈላጭ -ቆራጭ አገዛዙን ዘርግቶ ቆይቷል። የፀጥታው ተቋም መቶ በመቶ ከላይ እስከታች በወያኔ አባላትና ካድሬዎች ቁጥጥር ስር ያለ ሲሆን፤ የወታደሩ ተቋም የዋና ዋናዎቹ የአዛዥ

ቦታዎች ሆነ ከወታደሩ ተቋም ጋር የተያያዙ እንደ የመከላከያ ብረታ-ብረት ኢንጂኔሪንግ ኮርፖሬሽን (ሜቴክ) እንደሚባለው ዓይነተኛ ኢኮኖሚውን መዝረፊያ ቅርንጫፍ አካሎች በወያኔ አባላት የተያዙ ሲሆን፤ በሌላውም የወታደሩ ክፍል የወያኔው ድርጅት ድርሻ ከፍተኛ መሆኑ ይታወቃል።

የሽግግሩ መንግሥት የተወሰነ ኮሚሽን በማቋቋም፤ አንደኛ የወታደሩን ተቋም ይዘትና ተልዕኮ ማስተካከል ይጠበቅበታል። የወታደሩ ተቋም ነፃና ገለልተኛ የሚሆንበትን መንገድ ቀይሶ ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ ማዘጋጀት ይኖርበታል። በተመሳሳይ መልክ ፤ የፍርድ/የፍትህ ፣ የአስተዳደር ፣ ሌሎች ሌሎች ተቋማት፤ ከአንድ ቡድን ቁጥጥር ስር ለዘለቄታው የሚወገዱበትን መንገድ ያመቻቻል።

የሽግግር መንግሥቱ ሌላው ዐብይ ተግባር፤ በሕዝብ የተመረጠ ፓርቲ ወደ ሥልጣን ሊወጣ የሚችልበትን ሁኔታ ማመቻቸት እንዲሁም የምርጫ ሕጉን ማዘጋጀት፤ በማንም ድርጅት ወይም ቡድን ቁጥጥር ስር ያልሆነ ነጻ የምርጫ አስመራጭ ኮሚሽን የሚቋቋምበትንና በአጠቃላይም፤ ነፃና ርቱዓዊ ምርጫ ሊካሄድ የሚችልበትን ደንብና አሰራር ማዘጋጀት ይሆናል።

የሽግግሩ መንግሥት ከላይ ከተጠቀሱት ዓቢይ ተግባራት ውጭ በርካታ ሥራዎችና ኃላፊነት ይኖሩታል። የሽግግር ሂደት ተግባራትና ኃላፊነት ሊከናወኑ የሚችሉት፤ በሁለት ዋና ዋና አካላት አማካኝነት ነው። የመጀመሪያው የሽግግር ምክር ቤት ሲሆን፤ ሁለተኛው በዚሁ የሽግግር ምክር ቤት የሚሰየመው የአስተዳደሩን ሥራ የሚሰራው የሽግግር ጊዜ አስተዳደር ነው። የሽግግሩ ሂደት ሁሉም ሃሳቦች የሚበራዩበትና በውይይት፤ በምክክርና በድርድር እንዲሁም በሕዝብ ውሳኔ የጋራ ስምምነት ላይ የሚደረስበት ሲሆን፤ የሚቋቋመው ምክር ቤት፣ የሁሉንም ኅብረተሰብ ፍላጎት የሚያካትት ይሆናል። የተደራጁ የፖለቲካ ኃይሎች፤ የሙያ ማኅበራት ተወካዮች፤ የሀገር ሽማግሌዎች፤ ታዋቂ ግለሰቦች፤ የሃይማኖት አባቶች፤ እንዲሁም የሕዝብ ተወካዮች የሚሳተፉበት ይሆናል ።

የሽግግር ዘመንም በስምምነት የሚወሰን ይሆናል። ውይይቱና ስምምነቱ፤ እንዲሁም ሕዝበ-ውሳኔ የሚያስፈልጋቸው በርካታ ዐበይት ጉዳዮች የሚከናወኑበት ወቅት መሆን ስለሚችል፤ ምናልባት ከሁለት እስከ አራት ዓመታት ቢሆን ይመረጣል።

በሽግግሩ ሂደት ኅብረተሰቡ በመላ ተሳታፊ መሆን አለበት፤ ይገባዋልም። የሽግግሩ ሂደት ለዴሞክራሲያዊ ሂደት መንገድ ሊከፍት የሚችለው፤ ሕዝቡ ባጠቃላይ ተሳታፊ ሲሆን ነው። በአንድ ግለሰብ ወይም ቡድን መልካም ፈቃደኛነት ሊሄድ አይችልም። አይገባውምም - ይህ ዓይነት አካሄድም፤ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሳይሆን፤ ለአምባገነን ፈላጭ-ቆራጭ አገዛዝ በር መክፈቱን በታሪካችን ሁለት የታሪክ ማገናዘቢያዎች ስላሉን !

1) በ1967 ዓም የዐፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ሲገረሰስ ፤ የተደራጀው ወታደር ራሱን የሽግግር ኃይል አድርጎ ማቅረቡ የሚታወስ ሲሆን፤ ኢሕአፓ እንደ ድርጅት፣ ለሽግግሩ ሂደት የጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ጥያቄ ማቅረቡ ይታወሳል። በወቅቱ በትረ ሥልጣኑን የተቆጣጠረው ወታደራዊ ቡድን ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ብሎ ራሱን

ሲሰይም ኢሕአፓና ሰፊው ሕዝብ ተቃውም ቢያሰሙም፤ ሂሳዊ ድጋፍ በማለት ከደገፉት ጀምሮ አባሪና ተባባሪ በመሆን ያገለገሉትን ተጠቅሞ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግን ወደ ኢሰፓአኮ ከዚያም ወደ ኢሰፓ በመለወጥ ለአስራ ሰባት ዓመታት የፈላጭ ቆራጭ አገዛዙን አስፍኖ ሕዝቡን ለመከራና ለችግር የአገሪቱም ሉዓላዊነት አደጋ ውስጥ እንዲወድቅ አድርጓል።

2) በ1983 ዓም የደርግ መንግሥት ሲወገድም በወቅቱ አገዛዙን የጨበጠው የወያኔ ቡድን የበላይነትና ቁጥጥር የተካሄደውን ሽግግር አስመልክቶ፤ ኢሕአፓ ሂደቱ ወደ አምባገነንነት የሚያመራ ሽግግር መሆኑን ጠቁሞ ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሊያመራ የሚችለው አማራጭ የሽግግር መንገድ ምን እንደሆነ ቢያብራራም ወያኔ በምዕራባውያን ጌቶቹ ትብብርና ድጋፍ የይስሙላውን ሽግግር አካሂዶ ቁልፍ ቁልፍ የሆኑ መንግሥታዊ ተቋማትንና አካላትን በመቆጣጠር ለ27 ዓመታት ዘረኛና ከፋፋይ የሆነ አምባገነን አገዛዙን ለማስፈን በቅቷል።

ከዚህ በላይ ለመጥቀስ እንደሞከርነው የዘመኑና የወደፊቱ ተከታታይ ትውልዶች በአገራቸው ዘላለማዊ ሥርየት ሊያገኙ የሚችሉት ሥር-ነቀል የሥርዓት ለውጥ ተደርጎ ዴሞክራሲያ ሥርዓት እውን ሲሆን ብቻ ነው። ቀድም ብሎ በግልጽ እንዳስቀመጥነውም ይህ እውን ሊሆን የሚችለው በሥልጣን ላይ ያለው ቡድን በሕዝባዊ አመጽም ሆነ በሌላ የትግል ስልት ተገዶም ሆነ በሌላ ሁኔታ ሥልጣኑን እንዲለቅ ሲደረግና ሕዝባዊና ሁሉን አሳታፊ በሆነ ሰላማዊ የሽግግር ሂደት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን በአገራችን ለማስፈን ሲቻል ብቻ ነው። ከወቅቱ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሁኔታ መረዳት የምንችለው የኢትዮጵያውያን እድል ወሳኝ ደረጃ ላይ የደረሰ መሆኑን ነው። በአንድ በኩል ላለፉት ሦስት-አራት ዓመታት በተከታታይ በስፋት ሲካሄዱ የቆዩና በርካታ መስዋዕትነትን ያስከፈሉ ሕዝባዊ አመጾች አምባገነኑን አገዛዝ በማዳከም በኩል የተወሰነ ውጤት ሊያስገኙ የቻሉ ቢሆንም፣ ተጠናክረው ከቀጠሉ ፈላጭ ቆራጭነትን ጨርሶ ለማስወገድም ሆነ ዴሞክራሲን ለማስፈን ሰፊ እድል ያነገቡ መሆናቸው የሚታይ ነው። በሌላ በኩል አገዛዙ በሚወስዳቸው አስመሳይና የማማለል እርምጃዎች ታጋዩ ኃይል ተዘናግቶ እልህ አስጨራሽ ትግሉን ካቀዘቀዘ ወይም ትግሉን ካቋረጠ ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ ቡድን በአዲስ መልክ ታድሶና ተጠናክሮ የስቃይና የመከራ አገዛዙን ሊቀጥል የሚችልበት ሁኔታ ወለል ብሎ እየታየ ነው። ሁኔታውን በደንብ ተገንዝቦ ራስን ሳያዘናጉ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ ከታጋይ ኃይሉ የሚጠበቅ ቢሆንም የሕዝብ ትግልና ድል በጥገናዊ ለውጦች እንዳይጠለፉ ለመከላከልም ሆነ ትግሉ ተጠናክሮ የተፈለገውን ግብ እንዲመታ ለማስቻል የፖለቲካ ድርጅቶች የተለየ ኃላፊነት አለባቸው። በኢትዮጵያ አንድነትና ሉዓላዊነት በህዝቧ ዕኩልነት የሚያምኑ የፖለቲካ ድርጅቶች ከምንጊዜውም በላይ ኃይላቸውንና ክንዳቸውን ማስተባበር ያለባቸው ጊዜ አሁን ነው። የፖለቲካ ድርጅቶች የግል ፍላጎታቸውንና የሩቅ ጊዜ ዓላማቸውን በሁለተኛ ደረጃ አስቀምጠው የሕዝብን ትግል በመምራትና በማጠናከር በኩል ተገቢውን ሚና ከተጫወቱ፤ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች፣ የሙያ ድርጅቶች፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ ታዋቂና አገር ወዳድ ግለሰቦችና ሌሎች በተገቢው መንገድ ተሳትፎና ትብብር ካሳዩ የኢትዮጵያ ሕዝብ አምባገነንነትን ከጫንቃው ለማስወገድም ሆነ በሰላማዊ ሽግግር ዴሞክራሲያዊ መብቱን ሊቀዳጅ እንደሚችል አንዳችም ጥርጥር ሊኖር አይገባም።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !!

- የትውልድ ድልድይ የሚለው ቡድን በዋሺንግተን ዲሲ የኢትዮጵያ ኤምባሲ አዲሱን ጠ/ሚር ወደ ሰሜን አሜሪካ ሲመጣ ስለአቀባበሉ በተነሳው ሽኩቻ ሃዘኔታውን የገለጠበት የእንግሊዝኛ መግለጫ፤
  **The Press release at the Ethiopian Embassy in Washington DCregarding the reception of the Prime Minister fails its mark of integrity**

- ዲያስፖራዎች “መደመራችንን” በምን መልክ እናሳይ? አክሎግ ቢራራ (ዶር)

- **Rethinking the Ethiopian Transition: Identifying the sticky issues and prospects for reform**
  **Seid Hassan, Abu Girma, and Minga Negash**

- የሕዝባዊ ስብሰባ ጥሪ**ቅዳሜ**፣ ሐምሌ(July) 28 ቀን 2018
  ኢትዮጵያ በዴሞክራሲ ጎዳና፤ የተጀመረው ለውጥ፣ ተስፋዎቻችን እና ፈተናዎቹ በቤልጅየምና
  1. ክቡር አምባሳደር እውነቱ ብላታ....... የክብር እንግዳ
  2. ዶ/ር ነገደ ጎበዜ ---------------------- የውይይት ሃሳብ አቅራቢ
  3. ያሬድ ኃይለማርያም ------------------ የውይይት ሃሳብ አቅራቢ

- የሎስአንጀለስ ሐገር ወዳድ ኮሚቴ። የስብሰባ ቀን ( DATE) Saturday July 21, 2018

- ሃገርቤት ስለመግባት ወቅታዊ መግለጫ፣ የትግራይዴሞክራሲያዊትብብር(ት.ዴ.ት./TAND) - አረጋዊ በርሄ የወያኔ መሥራች የነበረው በቅርቡ ወደ ሀገር ቤት ከመሄዱ በፊት ያወጣው መግለጫ